# የሶቪዬት ህብረት እና የዩናይትድ ስቴትስ
# የልዕለ ሃያላኑ መንግስታት ብርቱ ምስጢራዊ ስብሰባ በአዲስ አበባ

(ትርጉም፡ በእሸቱ ጫቦ)

ከኢትዮጵያ እና ከሱማሌ ጦርነት እንዲሁም ከጂቡቲ ነጻ መውጣት ቀደም ብሎ በአዲስ አበባ የአሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ የሶቪዬት ህብረት እና የአሜሪካ (ዩናይትድ ስቴትስ) ዲፕሎማቶች የአደረጉት የምስጢር ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ (ማስታወሻ)

<u>የስብሰባው ማስታወሻ፡</u>

ከሚስተር ኤስ.ዋይ.ሲኒትስን ምስጢራዊ የዕለት ማስታወሻ፣ ቁጥር 2፣ ፈለግ ቁጥር 41፣ ፌብሩዋሪ 4፣ 1977 ዓ. .*

ስብሰባው የተካሄደው ከሚስተር ሔርበርት ማሊን በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ጉዳዮች አማካሪ ጋር ነበር… ፌብሩዋሪ 2፣ 1977

ዛሬ በአሜሪካ ኤምባሲ ሚስተር ማሊን ጋር ቀደም ብለን በተነጋገርነው (ቀጠሮ?) አገኘሁዋቸው (ተገናኘን)። የተወያየንባቸውና የጋራ ትኩረት ነጥቦች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

የኢትዮጵያን ሁኔታ በሚመለከት ሚስተር ማሊን ደርግን በሚቃወሙ ሃይሎችና በሱዳን በሚደገፉ በተለይ በስተሰሜን ምዕራብ የሐገሪቱ ክፍል ያለውን ውጥረት ግንዛቤ ውስጥ አስገብተዋል።

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበር (ጄኔራል) ተፈሪ በንቲ ስላደረጉት ንግግር ይዘትና በተለይ "ሃይለ-ቃል" አጠቃቀማቸው ሁኔታ ትኩረት ያለው ዕይታ (ግንዛቤ) እንዲደረግ አሳስበውኛል። ይኸውም ጸረ-ኢትዮጵያ ፖሊሲ የሚከተሉት የሱዳንና የሱማሌ መሪዎች ላይ ያተኮረ ነበረ። (ጃንዋሪ 21/30) ዘንድሮ በተጨማሪም ጄኔራል ተፈሪ በንቲ "ለተራማጅ ሃይሎችና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ህብረት" ያቀረቡትንም ጥሪ ያገናዝባል። ጥሪው አብዮቱና ለእናት (አባት) ሀገር በአንድነት ከጠላት መከላከልን የሚመለከት ነበር። ይህን ጥሪ በሚመለከት የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ) ስም (በቀጥታ) አልተጠቀሰም። በአሜሪካዊው ሚስተር ማሊን አስተያየት ኢ.ሕ.አ.ፓ ይህን የጄኔራል ተፈሪን ጥሪ የሚቀበለው አይመስላቸውም። ይህም ኢ.ሕ.አ.ፓ ደርግ ለሚከተለው ፖሊሲ ባለው ተቃውሞ ምክንያት ነው ብለው ያስባሉ።

ከዚህም ጋር ተያይዞ ይላሉ በመቀጠል፣ የተቃዋሚ ሃይሎች ህብረት የላቸውም። ባለው መንግስት (ደርግ) ላይ ያላቸው የተቃውሞ ህብረት የጊዜያዊነትና የታክቲክ ስልት (ጸባይ) አለው። የተቃዋሚ ሃይሎች ያለውን መንግስት ለመጣል (ለማስወገድ) ቢችሉ እንኳን በመሃላቸው የስልጣን ሽሚያ ሽኩቻው በግልጽ ይፈነዳል። በተለይ በተለይ ዘውድ ደጋፊ በሆነው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት (ኢ.ዴ.ሕ) በኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ) እና በሌሎች ግራ ክንፈኞች መካከል። በአሜሪካዊው አስተያየት የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በሀገሪቱ ኢትዮጵያ ብቸኛውና እርግጠኛ የጋራ የሆነ ብሔራዊ (ሀገር አቀፍ) ሃይል መሆኑ ይቀጥላል። ይህም የማይናቅ የሕዝብ ክፍል ድጋፍ አለማግኘቱ (ተቃውሞ መኖሩ) እንደተጠበቀ ሆኖ ነው።

ሌላው ምንም ጥርጥር የማያስነሳ (ግልጽ ጉዳይ) ቢኖር ሱዳንና ሱማሌ እንደሚሉት ሳይሆን፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በጎረቤት ሃገሮች ላይ "የጸብ ጫሪነት" እቅድም ይሁን ዓላማ እንደሌላት ነው። ለማንኛውም ግን በተውተበተበ (በተወሳሰበ) የሃገሪቱ የውስጥ

ችግር የተነሳ ለዚህ ጉዳይ ኢትዮጵያ ዕድልም ይሁን አጋጣሚው ይጎላታል። አቅሙም የላትም።

የደርግን (ምክር ቤት) ውስጡን በሚመለከት በቅርቡ በተደረገው የመዋቅር ማሻሻልና "የጋራ አመራር" ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ያለው አጠቃላይ ግምት "ደርግ ይበልጥ ለዘብ ያለ" ባህሪ ሊይዝ ይችላል የሚል ተስፋ ነው። ሆኖም ግን በቅርቡ ከ"ጄኔራል" ተፈሪ በንቲ ንግግር ሲገመገም ይህ ሆኖ አልተገኘም።

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲቀመጥ በአሜሪካዊው ዲፕሎማት አስተያየት ኢትዮጵያ ውስጥ ለመጭው ረዘም ያለ ወቅት (ዘመን) ሁኔታዎች መወሳሰባቸው ይቀጥላል። ውጥረቱም እንደዚሁ።

በአሜሪካዊው አስተያየት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ እየተባባሰ መምጣቱ በተለይ አረብ አገሮችና ሌሎች በጸረ-ደርግ ህብረት ካላቸው ተቃውሞና ለደርግ ተቃዋሚዎች ከሚያደርጉት ድጋፍ ባሻገር በሃገሪቱ የውስጥ ጉዳይ በቀጥታ ጣልቃ ከመግባታቸው ጋር ባብዛኛው ይቆራኛል።

ይህ ጉዳይ ሲጤን ይላሉ አሜሪካዊው ዲፕሎማት (ሚስተር ማሊን) - ጥያቄው ... ጭብጡ ... ኢትዮጵያ ተብሎ የሚታለፍ አይደለም። የአካባቢውን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያካትት ነው። በአንዳድ የአረብ "ቡድኖች" ዓይን ቀይ ባህርን ጠቅሎ በአረብ ቁጥጥር ስር ለማድረግ ፍላጎቱ አለ። ቀይ ባህር ደግሞ በጣም ቁልፍ ዓለ አቀፍ የባህር ትራንስፖረት ጉዳና (መስመር) ነው። ይህ ማለት በዚህ አካባቢ ከከባድ ውጥረት ባሻገር ጦርነት ሁሉ ሊቀሰቀስ (ሊነሳ) ይችላል።

ይህን ነጥብ በሚመለከት የኢትዮጵያንና የአሜሪካንን ግንኙነት ሁኔታ በተመለከተ፣ የወደፊት ክስተትና ዕድገት ሚስተር ማሊን የሰጡት አስተያየት የትኩረት ግንዛቤ ይሻል። አሜሪካዊው ዲፕሎማት በዚህ አካባቢና (በኢትዮጵያ) ጉዳይ በአሜሪካ በሚካሄደው የፕሬዚዴንት ምርጫ የተነሳ ጉዳዩን ክብደትና ትኩረት ነፍገነዋል/በቂ እና የሚገባውን ትኩረት ከአሜሪካን መንግስት አስተዳደር አላገኘም/ ብለዋል።

በ1974 ዓ. . በኢትዮጵያ ለውጥ ከተካሄደ በሁዋላ የአሜሪካ እና የኢትዮጵያ ግንኙነት ወሰብሰብ ያላና አወዛጋቢ እየሆነ ነው የመጣው።

የአሜሪካ መንግስት አልፎ አልፎ በኢትዮጵያ ቦግ የሚሉ የጸረ-አሜሪካ ተግባራትን ንቆ ማለፍ አይቻለውም። ለምሳሌም በቅርቡ በዚህ ዓመት 27/28 ጃንዋሪ 1977 ቀን አዲስ አበባ ውስጥ በተካሄደው ጸረ-ደርግ (መንግስት) የወጣቶች የተቃውሞ ሰልፍ ወቅት የዩ. ኤስ. አይ. ኤስ. (የአሜሪካ ህዝብ ግንኙነት) ህንጻ መስተዋት በተሰላፊዎች ከመሰበሩም ሌላ የጋዝ ቦንብ ተወርውሮበታል። ከዚህ በተጨማሪ የኢሕአፓ (የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ) በራሪ ጽሁፎች ታድለዋል። ተመሳሳይ ፈንጅም በአሜሪካ ወታደራዊ አማካሪ ተቋም (ማግ) ህንጻ ላይ ተወርውሯል።

በሌላ በኩልም በኢትዮጵያ መንግስት በተዘጋጀውና (ጄኔራል) ተፈሪ በንቲ ከላይ ቀደም ብለን የጠቀስነውን ንግግር ባካሄዱበት ወቅትም የተለያዩ አንደበተ ርዕቱ የሆኑ ተናጋሪዎች ጸረ-አሜሪካ ዲስኩርና ትርኢትም ታይቷል። /ከግንዛቤም አስገብተናል/ ጸረ-አሜሪካ መፈክሮችም ወዘተ ነበሩ። የሆነው ሆኖ ግን ግልጽ የኢትዮጵያ መንግስት መግለጫዎች የጄኔራል ተፈሪ በንቲን ንግግር ጨምሮ ቀጥታ ጸረ-አሜሪካ ትንኮሳ ቃና የላቸውም።

እንዲያም ሆኖ (ተያይዞም) ይላሉ ሚስተር ማሊን፣ የኢትዮጵያ መንግስት ከአሜሪካ መንግስት የተለያዩ ዕርዳታዎች ማግኘት መቀጠል የመሻት ምልክቶች ይታዩበታል።

በተለይ በተለይ ወታደራዊ ዕርዳታን በሚመለከት በተደጋጋሚ ዕርዳታው (የጦር መሳሪያው) መቼና እንዴት እንደሚመጣና የመሳሰለውን ጉዳይ በየጊዜው ይወተውታሉ።

በኢትዮጵያ ከተካሄደው የመንግስት ለውጥ ቀደም ብሎ አሜሪካ ለኢትዮጵያ የምታደርገው ወታደራዊ ዕርዳታ ደረጃው በየአመቱ ካስር እስከ አስራ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ነበር። ይህም የተለየ ትኩረትና "በወገንተኝነት" ያለማካካሻ ክፍያ ነበር። /መሳሪያ አቅርቦት፣ ተጓዳኝ ጥይት፣ ፈንጂ፣ መለዋወጫ፣ ወዘተ አካቶ።/

በቅርቡ ግን የአሜሪካ መንግስት ከሌሎች ሀገሮች ጋር ስላለው ወታደራዊ ትብብር ባወጣው አዲስ ፖሊሲ የተነሳ ለኢትዮጵያ የሚደረገው ወታደራዊ ዕርዳታ ወገናዊነቱን እንደጠበቀ ሆኖ ወደ መሸጥ (ግዢ) - ሽመታ - ተቀይሯል። ይህም ላቅ ያሉ ዘመናዊ መሳሪያዎችን ይጨምራል። በዚህ የተነሳም የዕርዳታው ደረጃ እርከን ጨምሯል። ይህም በመሆኑ በሁለቱ ሃገሮቻችን (ኢትዮጵያ እና አሜሪካ) መካከል በ1975 ዓ. . የተደረገው ውል (ስምምነት) የሚተልመው የጦር መሳሪያዎችን አቅርቦት፣ መለዋወጫዎቻቸውን፣ ተጓዳኝ ጥይትና ፈንጂ (አሙኒሽን) ዋጋ በግምት ወደ ሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ዶላር ያደርሰዋል። በዚህ ውል መሰረት በ1976 ዓ. . የአሜሪካ መንግስት ከመሳሪያዎቹ ከፊሉን አስረክቧል። ከቀረቡትም በርካታ "ፋንቶም" ተዋጊ አውሮፕላኖች ይካተታሉ። ዘንድሮም ተጨማሪ በርካታ "ፋንቶም" ተዋጊ አውሮፕላን አቅርቦት ይቀጥላል ተብሎ ታልሟል። በተጨማሪም አቅርቦቱ ኢትዮጵያ ባህር ሃይል፣ እንዲሁም የራዳር የአየር መቃወሚያን ይጨምራል።

አሜሪካዊው ዲፕሎማት አያይዘውም ሲናገሩ፣ አዲሱ የኢትዮጵያ መንግስት ተጨማሪ ወታደራዊ ዕርዳታ ከተለያየ አቅጣጫ የማፈላለግ ፖሊሲን ንቁ ሆኖ እያራመደ፣ እየተከተለ ነው። ይህንንም በተቻለ ሁኔታ ለራሱ (ለሀገሪቱ) ይበልጥ በተሻለና በሚጠቅም ቅይስ ነው። ይህም ቅኝት ሶቪዬት ህብረትን ይጨምራል። (አሜሬካዊው የ ኢትዮጵያ ወታደራዊ ልዑክ ቡድን በቅርቡ በዲሴምበር ወር ወደ ሞስኮብ ስላደረጉት ጉብኝት አጢነው ያውቃሉ (አልተሰወራቸውም)። በዚያውም ወደ ህዝባዊት ቻይና የተደረገውም ጉዞ አላመለጣቸውም። ሆኖም ግን ይላሉ፣ ቻይናዎቹ ለኢትዮጵያ የሚሆን "ብቁ" የረባ መሳሪያ የማቅረብ ችሎታ እንዳላቸው እጠራጠራለሁ ብለዋል።

የአሜሪካ መንግስት ይላሉ ሚስተር ማሊን፣ በአትኩሮት አዲሲቱ ኢትዮጵያ ስለመረጠችው የሶሻሊዝም ጎዳና ተቃውሞ የለውም፤ እንደቀድሞው (ፖሊሲያችን) የ ኢትዮጵያን ሉዐላዊነት፤ የሀገሪቱን ዳር ድንበር መከበርና የኢትዮጵያን አለመቆራረስ በጽኑ መመሪያነቱ እንቀጥልበታለን።

አሜሪካኖቹ በግልጽ መረዳት እንደተቻለው በአካባቢው የመረጋጋትና የሰላም ዋስትና ይሻሉ። ይህም በነጻ (ያለስጋት) በቀይ ባህር መርከቦቻቸውን (?የንግድ + የጦር) የማንቀሳቀስ ጉዳይ ነው። አግባብ ላለው ቁልፍ ለሆነ ጥያቄ ሲመልሱ በአሜሪካ እና በ ኢትዮጵያ መካከል በ1953 ዓ. . የተደረገው ስምምነት "የጋራ ደህንነት ዋስትና" የሚመለከተው የአሜሪካ መንግስት ለኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት የሚያቀርበውን ወገንተኛ የጦር መሳሪያ ዕርዳታ አቅርቦትና ተያይዞም "አንዳንድ የአሜሪካን ጥቅምና ፍላጎት" የመጠበቅ ዋስትና ነው ይላሉ። በቅድሚያ የሚጠቀሰውም በአስመራ የሚገኘው የአሜሪካ የግንኙት ማዕከል (ቃኘው) ነው። ያ በወቅቱ ለአሜሪካ ከፍተኛ ግምት/ዋጋ የሚሰጡት ነው። (ዛሬ ያ ማዕከል ተግባሩ ባብዛኛው ተከርክሟል/ተገድቧል)። ሚስተር ማሊን እንደሚረዱት /ያ ስምምነት/ የአሜሪካ መከላከያ ሰራዊት በቀጥታ የኢትዮጵያን ደህንነትና ሉዐላዊነት ለማስጠበቅ አይማገዱም። ለምሳሌም ይላሉ፣ ኢትዮጵያ ጦርነት ቢከፈትባት ሆነ የጦርነት ዛቻ ቢያሳስባትና የሀገሪቷ አንድነት ጥያቄ ስጋት ላይ ቢወድቅ የአሜሪካ መንግስትና ሰራዊት የውል ግዴታ የለበትም። የመተባበር እና ከጥቃት የማስጣል።

በኢትዮጵያ እና በሱማሌ መካከል እየተባባሰ የመጣውን የወቅቱን ሁኔታ በሚመለከት አሜሪካዊው እስከሚያውቁት ድረስ የአሜሪካ መንግስት ሁኔታውን ለማርገብ ሆነ ጸረ-ኢትዮጵያ የሆኑ የአረብ ሃገሮችን እንቅስቃሴ ለመግታት የወሰደው ዲፕሎማሲያዊ እርምጃ የለም። እንዲያውም የኢትዮጵያ መንግስትም ቢሆንም ይህን ጉዳይ በሚመለከት ለአሜሪካ መንግስት የአቀረበው ማሳሰቢያ የለም።

በአሜሪካዊው/ሚላን/ አስተያየት በአካባቢው የጦርነት መቀስቀስ ሊያስከትሉ ከሚችሉ የተዳፈኑ እሳቶች አንዱ የዘንድሮው የጅቡቲ ነጻ የመውጣት ጉዳይ ነው። የወደፊቱ የጅቡቲ አቅጣጫ በኢትዮጵያ እና በሱማሌ መካከል ይበልጥ የከረረ አለመግባባት ይፈጥራል። ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ ሱማሌዎች በጅቡቲው ጉዳይ ያላቸውን የፖለቲካ ጫና ድርሻ አልቀዋል። ከዚህም በላይ አሁን ካሉት የጅቡቲ መሪዎች ጋር የሱማሌ መንግስት ያለው የቅርበት ደረጃ ኢትዮጵያዊያንን በብርቱ አሳስቧቸዋል።

ጅቡቲ ከነጻነት በሁዋላ በኢኮኖሚውም ሆነ በፖለቲካው ዘርፍ የአረብ ሊግ አባል የመሆኗ ጥያቄ በጣም ግልጽ ነው /ማስረጃ አያስፈልገውም/።

የፈረንሳይ መንግስት ለቆ ሲወጣ የጅቡቲው ጉዳይ የባሰ ሊወሳሰብ እየተደገሰለት ነው። የአረብ ሀገሮች ተግተልትለው ቆንሱላ ካሁኑ ከፍተዋል። የአሜሪካ መንግስትም ከጅቡቲ ነጻነት ቀደም ብሎ ይህንን እርምጃ ይወስዳል። በቅድሚያ ግን የአሜሪካ መንግስት የፈረንሳይን መንግስት አግባብነት ያለው ፈቃድ ይሻል።

በውይይታችን ወቅት አሜሪካዊው በኢትዮጵያ እና በሶቪዬት ህብረት መካከል ስላለው ግንኙት ለማወቅ ግልጽ ፍላጎት እንዳላቸው ገለጹልኝ። የጉጉታቸውም መንስዔ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አንደኛ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር /ሻለቃ? ኮሎኔል?/ መንግስቱ ሃይለማርያም በቅርቡ ወደ ሃገራችን /ሶቪዬት ህብረት/ ጉብኝት ያደርጋሉ የሚባለው ጭምጭምታ ደርሷቸው ነው። ከዚህም በተጨማሪ በእሳቸው /ሚሊን/ ግምት በኢትዮጵያ እና በሶቪዬት ህብረት የሚፈጠር ቅርርብ ወዳጅነት የሶማሌ መንግስት በበጎ /በቀና መንፈስ/ እንደማይመለከተው ያክላሉ።

እኔ በበኩሌ ለአሜሪካዊው ግልጽ ያደርግሁላቸው በኢትዮጵያ እና በሶቪዬት ህብረት /ሩሲያ/ መካከል በጣም የቆየው የወዳጅነት ግንኙነት ይበልጥ የመጎልበት ዝንባሌ እንዳለው ነው። ለዚሁም ኢትዮጵያ እና የሶቪዬት መንግስት ጁላይ 14 ያወጡትን የጋራ መግለጫ ያጤኗል። ይህም በቅርቡ የኢትዮጵያ መንግስት ልዑካን በሞስኮ ያደረጉት ጉብኝት ውጤት ነው። የሶቪዬት ህብረት ለኢትዮጵያ የምታደርገው ቴክኒካል ትብብር ደረጃ ማደግ (የዩኒቨርስቲ መምህራን፣ የክህምና ባለሙያዎች፣ ወዘተ) እንዲሁም በአለፈው ዓመት አጋማሽ ላይ የሶቪዬት የኢኮኖሚ አማካሪዎች እዚሁ ያከናወኑት ስራ እና የመሳሰሉት። በግልጽ የተጠቀመው (በእኔ በኩል) በሁለቱ ሃገሮቻችን (ኢትዮጵያ እና ሶቪዬት) በከፍተኛ ደረጃ ግንኙነቱ የመቀጠሉ ነገር ከሁኔታው የሚጠበቅ የእድገት እርምታ መሆኑ ባያጠያይቅም ተግባራዊ አደራረጉ ግን በእቅድና በተጨባጭ ሁኔታዎች አፈጻጸም ጥያቄው አልተነሳም።

በተዛማጅም ሶቪዬት ህብረት በኢትዮጵያ እና በሶማሌ መካከል ያለውን አለመግባባት ጠንቅቀን እንደምናውቅ አስገንዝቤ የእኛ /የሶቪዬቶቹ/ የማያወላውል ጽኑ እምነታችን ግን በሁለቱ ሃገሮች መካከል በታቻለ መጠን መቀራረብ ፈጥረን ለችግሩ ሰላማዊ መፍትሄ ለመሻት መሆኑንና በጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት መክፈት እንዲችሉ ማብቃት ነው። ይህንንም ስንል በአካባቢው ያለው ሁኔታ ወደባሰ ደረጃ እንዳይዘቅጥ ከመሻት ጭምር ነው። ይህ አቋማችን በሱዳን እና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት እየተወሳሰበ መምጣቱንም ያካትታል። የወደፊት የኢትዮጵያና የሶቪዬት ግንኙነት ዕድገትና አቅጣጫ ሱማሌን ኢላማ እንደማያደርግ ግልጽ መሆኑን አስተኩሪያለሁ። የሱማሌ መሪዎች እንደሚያውቁት ከእነሱም ጋር ግንኙነታችን እና ወዳጅነታችን እያደገ እያለ

በመሆኑ ለኢትዮጵያ የቅርበታችን ማደግ ሊያሳስባቸው አይችልም፣ አይገባምም። እነሱም ወዳጆቻችን ናቸውና!

አሜሪካዊው ዲፕሎማት /ማሊን/ ያቀረቡልኝ ሌላው ጥያቄ በምን በምን ፈርጅ ነው የአሜሪካ ፍላጎትና ጥቅም በኢትዮጵያ ከሶቪዬት ህብረት ጥቅምና ፍላጎት ጋር የማይጋጨው የሚል ነበር።

እኔም የመለስኩላቸው፣ በእኔ አሰተያየት፣ ዋናውና መሰረታዊው በመርሆና በተግባር ደረጃ መካሄድ ያለበት ፖሊሲ የኢትዮጵያን ሉዐላዊነትና የግዛት አንድነት ማክበር፣ በሃገሪቱ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት፣ እንዲሁም በሃገሪቱ ውስጥ በመካሄድ ላይ ባለው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ህዝብ አቀፍ ለውጥ በሚመለከት ከተጨባጭ ከሃገሪቱ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ (የተስተዋለ) እይታ መውሰድ አልኳቸው። ተያይዞም የሰላም ግንባታ እና የጦርነት ስጋት ውጥረትና ግጭት በአካባቢው ሃገሮች እንዳይካረር መግታት፣ እንዲሁም በቀይ ባህር ላይ ማናቸውም ማዕቀብ የሌለበት ነጻ የባህር ጎዳና አድርጎ የማቆየት መርሆ አጥብቆ መከተል። ይህም ተቀባይነት በአገኙት ዓለማ አቀፍ ህጎችና በአጠቃላይ ለሰላማዊ ግንኙነት ሲባል።

ለውይይቱ ስለመጣሁ አመስግነውኝ የአሜሪካው ዲፕሎማት (ሚስተር ማሊን) ለወደፊቱም የዚህ አይነት ግንኙነትና የሃሳብ መለዋወጥ እንዲቀጥል እንደሚሹ ገልጸው በተነሱት ነጥቦች ዙሪያ እሳቸውም ሙሉ በሙሉ እንደሚስማሙ ሃሳባቸውን ይፋ አደረጉ።

ኤስ. ኤስ. ሲኒቲስን
ኮንሱላር ሚኒስትር
በ ኢትዮጵያ የሶቪዬት ህብረት ኤምባሲ

---

* በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሱት ዓመተ ምህረቶች በሙሉ በፈረንጅኛው ናቸው

<u>ከተርጓሚው ማስታወሻ</u>

- ይህ ሰነድ በአሁኑ ወቅት ምስጢራዊነቱ ቢያበቃም ስለትላንቱ እንጅ ዛሬ ደግሞ ምን እንደሚመካከሩብን እነሱም አይነግሩም፣ እኛም አናይም። ታውረን!
- ሊጠን የሚገባው በባላንጣነት የሚፈላለጉት መንግስታት ተወካዮች በሀገራችን ጓዳ ሲወያዩ፣ ለእኛ ብለው ሳይሆን "ለመሆኑ የሚያጣላን ወይ አክሮ ሊያጋጨን የሚችል ነገር እዚህ ቤት ምን አለ?" ብለው ነው።
- ፈረንጆቹስ፣ አረቦቹም፣ ሌሎቹም ሌሎቹም የየራሳቸውን ሃገር ቢወዱ ማለፊያ ነው! የእኛዎቹና እና ጎረቤቶቻችን የሰው መፈክር ተሸካሚ የመሆኑ ፋይዳ እና ጭዳነት እስከ መቼ ይቀጥል ይሆን?!
- የሱማሌ ሪፑብሊክ ወንድሞቻችን ዛሬ የወደቁበት አዘቅት በሰብአዊነትም ባፍሪካዊነትም በጣም የሚሰቀጥጥ እና የህሊና ቁስል ነው። ያልፋል! የማያልፍ የለምና! ዓይናችንን በፈቃደኝነት ካልጨፈንን ለእኛም የጠላትን ምክር መስማትን ክፉ ውጤት ያሳየናል።
- ይህ ጽሁፍ ወደ አማርኛ የተመለሰበት ዋናው የእንግሊዝኛው በተከታዮቹ ገጾች ቀርቧል።
- በተቻለኝ አቅም የእንግሊዝኛውን ሰነድ ከእነ ዲፕሎማሲያዊ ቃናው ጭምር ወደ አማርኛችን ለመመለስ ጥሪያለሁ፣ ስህተቶች ቢገኙ ካቅም ማነስ መሆኑን በትህትና እየገለጽኩ፤ ለማመሳከሪያነት ኦሪጂናሊ የእንግሊዝኛውን ቅጂ አባሪ ያደረግሁትም ለዚሁ ነው።

እሸቱ ጫቦ ከለንደን፣ ኢሜል አድራሻዬም፡ addisminch@hotmail.co.uk

Memorandum of Conversation between Soviet Counselor-Minister in Ethiopia S. Sinitsin with Political Counselor of the U.S.. Embassy in Ethiopia Herbert Malin, 2 February 1977

From the diary of SECRET, Copy No. 2
S.Y. Sinitsin 4 February 1977
Ser. No. 41

NOTES OF CONFERENCE
with Advisor for Political Issues
of USA Embassy in Ethiopia
HERBERT MALIN
2 February 1977

I met today with Malin in the USA Embassy by preliminary arangement. The following points of interest were discussed.

Concerning the situation in Ethiopia, Malin noted the tension of the situation caused by the activation of forces opposed to the Derg, especially in the northwestern region of the country which is siding with the Sudan. He directed attention to the "harsh pronouncements" of the Chairman of the PMAC, Teferi Banti, of January 29 and 30 of this year, addressed to the leaders of the Sudan and Somalia, who are pursuing an anti-Ethiopian policy, as well as to his call for a union of "all progressive and patriotic forces" for the defense of "the revolution and the fatherland," in this connection not mentioning the anti-government leftist organization "Ethiopian People's Revolutionary Party" (EPRP). However, Malin feels that the EPRP will hardly agree to support the call of Teferi Banti, due to its disagreement with the policy of the Derg.

At the same time, he continued, the opposition forces are not united and their joint opposition to the existing regime has a temporary and tactical character. Even if the opposition forces should succeed in overthrowing this regime, a struggle for power will erupt between them, especially between the pro-monarchy "Ethiopian Democratic Union" and the "Ethiopian People's Revolutionary Party" and other leftist groups. The PMAC, in his opinion, continues to be the only real common national power in contemporary Ethiopia, although its policy does not enjoy support among a significant portion of the population. It is further undoubted that, despite the declarations of the Sudanese and Somalis, present day Ethiopia does not harbor "aggressive designs" in relation to its neighbors, and in any event lacks the opportunity for the same in view of its complex internal problems.

Concerning circumstances in the Military Council itself, after the implementation of its partial reorganization in the end of December [1976] with the aim of reinforcing "collective leadership" of the country, the opinion predominates in Addis Ababa that the policy of the PMAC will acquire a "more moderate" character. However, to judge by the declarations of Teferi Banti, that has not occurred.

In sum, according to Malin's opinion, circumstances in Ethiopia will continue to be complicated and tense for a long time to come.

For his part, he noted that the deterioration of existing circumstances in the country is tied in significant part to the open interference in the internal affairs of Ethiopia by the community of Arab countries and other forces, who are aligned in hostility to the policy of the PMAC and are supporting forces opposed to it. He noted further that, in the final analysis, what is at issue is not merely Ethiopia itself, but the situation in the region as a whole, the efforts of certain Arab circles to establish complete control over the Red Sea, which constitutes an important international maritime route, and the possible eruption here of a completely tense situation and even armed conflict. In this connection the opinion of Malin on the condition of American-Ethiopian relations and prospective development of circumstances in the given region was of interest.

Malin said that until now the American administration, owing to the presidential elections, had not had an opportunity to involve itself to the extent warranted in the development of its policy in this region. Since the change of regime in Ethiopia in 1974, American-Ethiopian relations have had a relatively complex and contentious character. The USA cannot ignore the periodic outbreaks of anti-American activity in the country. Thus, on 27-28 January of this year, in the course of anti-government demonstrations by young protesters in Addis Ababa, glass was broken and gas bombs were hurled at the department of the USIS [United States Information Service] building, in addition to which leaflets of the "Ethiopian People's Revolutionary Party" were distributed. Similar bombs were hurled at the building of the MAAG [American Military Advisory Group]. In the course of a demonstration of by a group organized by the Military Council on 3 January in Addis Ababa in connection with the above-noted pronouncements of Teferi Banti, anti-American performances by an array of orators were also seen, along with anti-American placards and so forth, although official declarations, including those by Teferi Banti himself, contained no such direct anti-American missives.

At the same time, Malin continued, the Ethiopian government displays an interest in continuing to receive various forms of assistance from the USA, especially military assistance, and frequently talks about the timetable for the delivery of military supplies and so forth. Prior to the change of regime in Ethiopia, American military assistance was at an annual level of 10-12 million American dollars and was administered preferentially on an uncompensated basis (deliveries of arms, ammunition, spare parts, etc.). In recent years, owing to the new policy of the USA in the area of military cooperation with foreign governments, American military assistance to Ethiopia has been granted preferentially on commercial terms, and it includes several types of more advanced armaments, in connection with which the value of the assistance has grown. Thus, the signing of a multi-year contract in 1975 envisions the supply of armaments, spare parts and ammunition in the approximate sum of 250 million American dollars. Already in 1976 the USA supplied Ethiopia with part of those arms, including several "Phantom" fighter planes. This year a supply of several additional fighter planes is contemplated, as well as supplies for the Ethiopian navy, and radar defenses.

Malin noted further that the new Ethiopian administration is pursuing a policy of seeking methods of receiving military assistance from other sources as well, possibly on terms more advantages to it, including from the USSR (he is aware of the visit by the Ethiopian military delegation to Moscow in December of 1976), as well as the PRC [People's Republic of China], although he doubts that the Chinese are capable of supplying Ethiopia with "serious armaments."

The USA, Malin emphasized, does not oppose the "socialist choice" of new Ethiopia and, as before, firmly supports the principal of respect for its territorial integrity, and is against the partition of Ethiopia. The USA, it is understood, is interested in the guarantee of stability in that region and freedom of navigation in the Red Sea.

Responding to pertinent questions, he said that the American-Ethiopian agreement of 1953 "on mutual security guarantees" concerned the preferential supply of assistance by the USA to the armed forces of Ethiopia and the guarantee of "certain American interests," first and foremost of which was the operation of the "center of communications" in Asmara, which was of great importance at the time (that center has now been curtailed in significant part); but, as he understands it, [the agreement] does not call for the direct involvement of American armed forces in the defense of Ethiopia's security, for example, in the case of aggression against it or a threat to its territorial integrity.

Concerning the present deterioration in Ethiopian-Somali relations, as far as Malin knows, the USA has not undertaken any diplomatic steps toward its normalization or restraint of anti-Ethiopian actions by the Arab countries, and in fact the Ethiopian government itself has not raised the issue with the USA.

One of the potential sources for an eruption of a conflict in that region, in Malin's opinion, is the independence of Djibouti that has emerged this year, inasmuch as a serious disagreement exists between Somalia and Ethiopia regarding the future policy of Djibouti. In recent months, the Somalis have succeeded in reinforcing their political influence in Djibouti, and their ties with its present leaders, which has seriously worried the Ethiopians. It is evident, as well, that after its declaration of independence, Djibouti will enter the League of Arab Nations, both in political and

economic respects, inasmuch as the position of Djibouti will be complicated following the departure of the French. An array of Arab nations has already established consulates there. The USA also intends to do this prior to the declaration of independence, having requested appropriate permission from the government of France.

In the course of the discussion, Malin expressed interest in the state of Soviet-Ethiopian relations, having come upon rumors concerning the upcoming visit to the USSR of First Deputy Chairman of the PMAC Mengistu Haile Mariam, and also in connection with the negative, as he understands it, attitude of Somalia toward the prospective development of Soviet-Ethiopian cooperation.
I told Malin that our traditionally friendly relations with Ethiopia have a tendency to develop further, as evident from the joint Soviet-Ethiopian communique of 14 July 1976, resulting from the visit to Moscow of an Ethiopian state delegation; the growth of Soviet technical assistance to Ethiopia (teachers in the University, doctors, etc.); the work here during the second half of last year by Soviet economic experts, and so forth. It was pointed out that the continuation of contacts between the two countries at a high level would be the natural procedure under such conditions, although, however, that question had not come up in respect to a concrete plan. I said further that we are aware of the disagreements between Somalia and Ethiopia, and that our unwavering position in that connection is to serve as a motivation for both countries to move towards a peaceful resolution of these disagreements at the negotiating table, in order to prevent a deterioration of circumstances in this region. This relates as well to our position in connection with the current complication in Sudanese-Ethiopian relations.. As concerns the future of developments in Soviet-Ethiopian cooperation, it is understood that this cannot be directed against Somalia, with whom we are also developing friendly relations, as the Somali leadership is well aware.
Malin asked, in my opinion, in what spheres would the interests of the USA in Ethiopia not be counter to the interests of the Soviet Union.

I replied, that in my view, these spheres would first and foremost encompass the conduct of a policy of respect for the sovereignty and territorial integrity of Ethiopia; noninterference in its internal affairs; a realistic approach to the social-economic and political transformations taking place in the country by the will of the people; the building of peace and security and a halt to the growth of tensions and conflicts between the countries of that region; and adherence to the principle of unrestricted navigation in the Red Sea, in accordance with recognized standards of international law and the interests of peaceful relations in general.

Thanking me for the conference, Malin expressed a desire for continuation of further contacts and exchanges of opinions regarding the questions discussed, as to which, for his part, he stated his agreement.

COUNSELOR-MINISTER TO THE USSR EMBASSY IN ETHIOPIA
/s/ S. SINITSIN